# የጋራ ችግሮቻችንን በጋራ ለመፍታት

**መጋቢት 19፣ 2001**

የኢትዮጵያ ህዝብ፣ የጭቆና መዋቅር ከዘረጋበት፣ የብሔራዊ ጥቅሙን አሳልፎ ከሚሰጥበት እና መብቱን አፍኖ ከያዘበት የመለስ መሰተዳዳር ተላቆ፣ ዴሞክራሲና የህግ የበላይነት የሰፈነባት አዲሲቷ ኢትዮጵያን ለመገንባት ይፈልጋል። የአዲሲቷ ኢትዮጵያ መሰረትም የህዝቦች የምርጫ መብት፣ የሰብአዊ መብት፣ እኩልነት፣ የእኮኖሚ ደህንነት፣ እና የብሔራዊ ጥቅም የሚከበሩበተ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ሥርዓት እንዲሆን ይሻል። ህዝቡ የተጫነበትን መሰተዳድር ለማስወግድ ብርቱ ፍላጎቱ መሆኑን በይፋ ካሳወቀና ለአደዲሲቷ ኢትዮጲያ ግንባታም ሲታገል፤ ትግሉም የሚጠይቀውን መሰዋትነት የመክፈለ ሂደትን ከተያያዘው ሁለት አሥርታት ሊሞላው ነው። ይሁን እንጂ፣ የትጉሉ ሂድት ውጤት ሊያመጣ ቀርቶ ወደግቡም የተጠጋ አይመስልም። በርግጥ በግንቦት 1997 ምርጫ ሂደት ተያይዞና በሱም ዋዜማ የተሰፋ ጭላጫል ታይቶ ነበር። የህዝባዊ ድል መቃረብ አስበርግጎት የመለስ ቡድን የወሰደው የአፈና እርምጃ ትግሉን እንደገና አድክሞታል። በሀገረ ውስጥም ሆነ በውጭ የትግሉ ደጋፊዎችና አንቀሳቃሾች የሆኑት አያሌ የተቃዋሚ ቡድኖችም መለስተኛ ቅራኒያቸውን ወደ ኋላ በመተው መሰረታዊ ህዝብዊ ጥያቄዎች ላይ በማተኮርና ሃይላቸውን አሰተባብረው ለመታገል ባለመቻላቸው ለትግሉ መዳካም የየራሳቸውን አሰተዋጾ ያደረጉ ይመስለናል።

## ረሀብ፣ ድህነት እና የዋጋ ግሽበት

ትግሉ በመዳከሙ ምክንያት የመለስ ቡድን ለእራሱ ጥቅም ለአቋቋማቸው ካምፓኒዎችና አጫፋሪዎቹ ለሆኑ ለጥቂት ሀብታሞች ገሃድ በሆነ መልክ የሚያዳላውን የኢኮኖሚ ፖሊሲን ተግባራዊነት ለማሰቆምና ለህዝቡ መሰረታዊ የኢኮኖሚ ችግርች እልባት ማገኘታ፣ በምግብ እራስን በመቻል በአጠቃላይም ለኢኮኖሚ ዕደገት እንቅፋት የሚሆኑ ነገሮችን ሁሉ በማሰወገድ ላይ ያተኮረ የልማት ፖሊሲን ለማራመድ አልተቻለም። ይህም በመሆኑ መለስና ባለሥልጣኖቹ ለብዙ አመታት በያመቱ ከፍተኛ የኢኮኖሚ ዕደገት ተግኝቷል ቢሉም ከአሥር ሚሊዮን በላይ የሚቆጠር የሀገራችን ህዝብ ከረሀብ ወጥመድ አልወጣም። የዕለት ጉርሱን የሚያገኘው ከውጭ ዕርዳታ ነው።፡ ሰፊ ተቃባይነት ባለቸው የድህነት/የእጦት መስፈርቶች መሰረት በዛሬይቱ ኢትዮጵያ በገጠርም ሆነ በከተማ በድህነት አዝቅት ውስጥ የወደቀው ከሀገሪቷ ህዝብ ከግማሽ በላይ መሆኑን አያሌ ጥናቶች ያመለክታሉ። እየናረ የመጣው የዋጋ ግሽበት ያስጨነቀው ኢትያጵያዊም በሚሎዮን የሚቆጠር ነው።

በአሁን ወቅት የተጠናወተውን የኢኮኖሚ ቀውስ ለመቋቋም በሚል ሰብብ የመለስ ቡድን በዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅት ድጋፍ በሀገር ውስጥ የነዳጅ ዋጋ እንዳይንር የሚስጥ ድጎማን፣ ኢኮኖሚን ለማሰደግ የሚሰጡ ብድሮችንና ሌላም የህብረተሰብን አባላት ሊጠቅሙ የሚችሉ ፖሊሲዎችን አ. አ. ከ2008/2009 በጀቱ ውስጥ እንዳይጠቃለሉ አድርጓል። ይህ እርምጃ መላውን የኢትዮጵያን ህዝብ በተለይም ድሀውን ክፍል ለባሰ ችግር የዳረገው መሆኑን የተለያዩ መረጃውች ይጥቁማሉ። በቅርቡ ከሽህ በላይ ለሚቆጠሩ ሠርተኞች የገቢ ምንጭ የነበረው የኮካኮላ ፋብሪካ በውጭ ምንዛሬ እጥረት ምክንያት መዘጋት፣ በድሬደዋ የባቡረ ሀዲድ ሠረተኞች

የሥራ ማቆም አድማ መምታት፣ በከተሞች ሁሉ የምግብ ሸቀጦች ዋጋ መናር የችግሩ መባባስ የሚከሰትባቸው ድርጊቶች ናቸው። እንዚህ ኢከኖሚያዊ ችግርች ከሌሎች ችግርች ጋር ተዳምረው ህዝቡን ለባሰ ችግር አጋልጠውታል።

## ማህበራዊና ፖለተካዊ ችግሮች

የመለስ መስተዳድር መቀጠል የኢኮኖሚ ችግሮችን ብቻ ሣይሆን ማህበራዊ ችግሮችንም አባብሷል። ህዝባችን ለአያሌ አመታት ተቻችሎ የኖረ ቢሆንም ባለፉት የቅርብ ዓመታት ውስጥ እየተስፋፉ የመጡ የጎሳና የሌሎችም ማህበራዊ ግጭቶች ሰለባ ሆኗል። ለምሳሌ የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ጉባኤ (ኢሰመጉ) ባለፌው ዓመት ማክተሚያ ወራት ባወጠው ዘገባ በዚያው ዓመት የጎሳ ግጭቶች መሰፋፋታቸው፣ በብዙ መቶዎች የሚቀጠሩ ግለሰቦች መገደላቸውን፣ በብዙ መቶ ሺህ የሞቆጠሩ ከኑሮአቸውና ከመኖሪያ ሰፈራቸው የተሰደዱ፣ ንብረታቸው የወደመ መሆኑን በዝርዝር መረጃ የተደገፈ ዘገባ አቅርቧል። በቅረቡም በቦረና በኦሮሞና በሱማሌ ጎሳዎች መካክል ተፍጥሮ በነበረ ግጭት ምክንያት አያሌ ሰዎች ሕይወታቸው ማለፉ፣ 70 ሽህ አካባቢ የሚሆኑ ግለሰቦች ከመኖሪያ ሰፈራቸው መፈናቀላቸው በብዙ የመገናኛ አውታሮች በሰፋት ተዘግቧል። ባለፈው የካቲት ወር (2009) ይፋ የሆነው የዩናትድ ስቴትስ አሜሪካ ዓመታዊ የሰብአዊ መብት ዘገባም በኢትዮጵያ በጦርነትና በጎሳ ግጭት ምክንያት 200 ሽህ የሚሆኑ ሰዎች ከኑራአቸው የተፈናቀሉ መሆኑን ጠቅሷል። ለአፍሪካ የእርስ በርስ ግምገማ እንዲያዘገጅ የመለስ መሰተዳደር እራሱ የሰየመው የጥናት ቡድን በጃናዋሪ 2009 ይፋ ያደረገው ዘጋባ በጎሳ ግጭት ምክንያት አያሌ ሰዎች መፈናቀላቸውና በኢትዮጵያ ብዙ የክልል አሰተዳዳሪዎች የጎሳ ግጭቶችን የሚለኩሱና የሚያቀጣጥሉ መሆኑን አትቷል፤ ለግጭት መፍትሄ እንዲፌለጉ የተቋቋሙ ኮሚቴዎችም ተመሳሳይ ጸረህዝብ ድርጊት እንዲሚያካሄዱ ገልጿል።

ከኢኮኖሚና ከማህበራዊ መስኮች በተጨማሪ፣ በሀገራችን የመለስ ቡድን ጸረ-ህዝብና ጸረ-ዕድገት ድርጊት በተቃዋሚ የፖለቲካ ቡድኖች እንቅስቃሴንና የስብአዊ መብቶችን በማፈን ላይ ያነጣጠረ እርምጃ ነው።የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ጉባኤ (ኢሰመጉ) የቅርብ ጊዜ ዘገባዎች፣ ስለኢትዮጵያ ለአፍሪካ የውስጥ ጉዳይ ግምገማ መሰረት እንዲሆን የቀረበው ሰነድ እና የዩናትድ ስቴትስ አሜሪካ ዓመታዊ የሰብአዊ መብት ጥንቅር ይህንን ጸር-ህዝብ ድርጊት በሰፋት አቅርበውታል። ለምሳሌ፣ 1) የመለስ አሰተዳደር ከ1997 ምርጫ ወዲህ ለተቃዎሚዎች የተቃዋሞ ስለፍ ፍቃድ በፍጹም አልሰጠም፤ ስብሰባም አይፈቅድም፤ ከተፈቀደም በአድራሽ ውስጥ እንጂ በአደባባይ አይደለም፤ 2) በየክልሎቹ የመንግሥት በላሥልጣኖች ተቃዋሚዎች ቢሮ እንዳይከፍቱ ይከለክላሉ፣ የተከፈቱትንም ቢሮዎች እንዲዘጉ ተጽእኖ ያደርጋሉ። የቢሮ አካራዮችን ያስፈራራሉ፤ 3) የመንግሥት የጸጥታ አካላት የተቃዋሚ አባላትን ይግደላሉ፣ ይደበድባሉ፣ ያስራሉ፤ 4) የመለስ መሰተዳደር የፕሬስ ነፃነትን ለማፈን በወሰደው እርምጃ አያሌ ጋዜጠኞች ታሰረዋል፣ በገፍ እንዲሰደዱ ተገደዋል፣ ተንገላተዋል፣ የማሰፈራራት ድርጊት ተፈጽሞበቸዋል፣ 5) የሀገራችን ከያኒያን እና ድምፃውያንም ከሰለባነት አልዳኑም፣ የአሜሪካው የሰብአዊ መብት ሪፖርት በትክክል እንዳመለከተው በተለይ ከ1997 ምርጫ በህዋላ የመለስ መሰተዳዳር ዘፈኖችን እንደተቃዋም ድርጊት የሚያይ መሆኑ ይፋ ሆኗል። ስለዚህም አፈናውን በሰፋት ተያይዞታል፤ እኛ በግለጽ እንዲሚገባንና በጃንዋሪ 2009 ባወጣነው መግለጫችን

*እንዳሰፈርነው፣ እንዲሁም የዚህ ዓመት የአሜሪካ የሰብአዊ መብት ዘገባም እንደሚያመለክተው የቴዲ አፍሮ መታሰር ከዚሁ የኪነጥበብ አፈና ጋር የተያያዘ ነው።*

## ***ትግላችንን እናሰተባብር***

***በአጠቃላይ በሀገራችን ረሀብንና ድህነትን  ለማሰወገድ ቅዲሚያ የሚስጥ ፖሊሲ የሚያራምድ እና ለማራመዱም ህዝባዊ ቁጥጥር የሚደረግበት ህዝባዊ መሰተዳደር እንዳይመሰረት የመለስ ቡድን አፍኖ ይዟል። ሁኔታው በዚህ ከቀጠለ ችግሮች የበለጠ እንደሚባባሱ ይገመታል።ምን እናድርግ? እኛ በቶሮንቶ ካናዳ የኢትዮጵያዊያን ተቆርቋሪ ኮሚቴ አባላት ህዝባችን ባለዘርፈ ብዙ ችግሮችን እንዲያስወግድና የሰብአዊ መብት የሚከበርበት ህዝባዊ መሰተዳደር እንዲመሰርት የምንችለውን ሁሉ ድጋፍ የመሰጠት ሃላፊነት ያለብን መሆኑን እናምናለን። ሃለፊነታችንን ከምንወጣባቸው ተግባራት መካከልም የህዝባችንን ብሶት ለፓርላማ ተወካዮች፣ ለዓለም ህብረተሰብ አባላት እና ለመግስታት ለማሰማት ሰለማዊ ሰልፎችንና ህዝባዊ ሰብሰባዎችን ማካሄድ፣ የሚደርስበትን የሰብአዊ መብት ረገጣን የሚመለከቱና የሚያወግዙ መግለጫዎችን፣ በራሪዎችንና ሌሎችንም መሰል ጹፎችን ማሰረጨት መሆኑን እናምናለን።***

***በሀገራችን በተቃዋሚ የፖለቲካ ደርጅት መሪዎች፣ አባላቶቻቸውና ደገፊዎች ላይ የሚካሄደው አፈና ሳይገታ፣ እነዚህ ድርጅቶች ህዝባችን የገጠመውን ችግር እንዴት እንዲሚፈቱ ለህዝብ በይፋ የሚያቀርቡበት በቂ ጊዜና ሁኔታ ሳይኖር፣ የሀገራችን የተለያዩ የህብረተስብ ክፍሎች፣ ለችግሮቻቸው መፍትሄ ማግኘት ይረዳናል የሚሉትን የፖለቲካ ፓርቲ ፖሊሲን የመምረጥ መብታቸውን ተነፍገው፤ በአጠቃላይም ህዝባዊ ዴሞክራሲ ታፍኖ የሚካሄድ ምርጫ ሁሉ ህዝባዊ ችግርን የሚፈታ ሥርዓት ይፈጥራል ብለን አናምንም። የዘህ ዓይኑቱ አፈና የሰፈነበት ምርጫ በዕውነተኛ ይዘቱ ወያኔና ደጋፊዎቹ በብቸኝነት የሚወዳደሩበት በውጤቱም የወኔ የአፈና አሰተዳዳር በምርጫ ስም እድሜውን የሚያራዝምበት ይሆናል ብለን እናምናል። በመሆኑም ተቃዎሚዎች ሁሉ ምርጫውን በርግጥ ህዝባዊ ምርጫ ለማድረግ የሚያሰፈልጉ መብቶች በቅዲሚያ እንዲከበሩ ታግለው እንዲያታግሉ፣ ህዝቡም የተገፈፈውን መብት እንዲያሰመልስና ለውደፊትም በባለቤትነት መብቱን ለማስከበር እንዲችል እንዲቀሰቅሱትና እንዲያሰልፉት፣ አሰላለፉም በተናጠል ሳይሆን በህብረት፣ በትብብረና በመደጋገፈ ላይ ያተኮረ፣ በሁለተኛ ደረጃ በሚታዩ ችግሮች ወይም መግባቢያ ጉዳዮች ላይ ሳይሆን በመሰረታዊ ሀገራዊና  ህዝባዊ አንደነት ላይ የተመሰረተና በዴሞክራሳዊና ሰብአዊ መብቶች መከበር ላያ ያነጻጸረ እነዲሆን ጥሪ እናቀርባለን። በዚህም ትግል ውጤት ለማምጣትም ተቃዋሚ ሃይላት ትግላቸውን እንዲያሰተባብሩ እናሳስባለን። እኛም በበኩላችን ያለብንን ሀላፊነት ለመውጣት በየግል መሯሯጥ የሚፈለገውን ውጤት እንደማያሰገኝልን ስለምንገነዘብ፣ በሀገራችን ሥር ለሰደደው ባለዘርፈ በዙ ችግር መፍትሄ ሊገኝና የሰብአዊ መብት ሊከበር የሚችለው በጋራ፣ ሃይላችንን አሰተባብረን ስንታገል መሆንኑ ስለምናምንበት ከሌሎች ወገኖቻችን ጋር ትግላችንን ለማሰተባበር የሚንጥር መሆኑን እንገልጻለን። በጋራ ትግሉ የሚያምኑ ወገኖቻችንም ይህንኑ ትብብር ተግባራዊ እንዲያደርጉት ጥሪ እናቀርባለን።***

***በቶሮንቶ ካናዳ የኢትዮጵያዊያን ተቆርቁዋሪ ኮሚቴ ሥራ አስካሂያጅ***
***ቶሮንቶ፣ ካናዳ***